Immigratie- en Naturalisatiedienst
*Ministerie van Justitie en Veiligheid*

# የመግባት እገዳ ወይም መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ የሚተላለፍ ውሳኔ ለኣንተ ምን ትርጉም አለው?

የመግባት እገዳ እንደተወሰነልህ ብቻ ወይም መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ ብቻ ውሳኔ ተሰትጥቶሃል። ወይ የመግባት እገዳ እና መረጃህን ደግሞ በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ ውሳኔ ተሰጥቶሃል። በደረሰህ የውሳኔ ጽሁፍ ውስጥ ለምን እንዳትገባ እንደታገድክ ወይም መረጃህን ለምን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ እንደተወሰነ ተገልጿል። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የመግባት እገዳ ወይም መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ የተላለፈውን ውሳኔ ምን ማለት እንደሆነ እና ይህ ላንተ ምን ትርጉም እንዳለው ማንበብ ትችላለህ።


1. የመግባት እገዳ ምንድን ነው?
2. በመረጃ ስርዓት ውስጥ መመዝገብ ምንድን ነው?
3. የመግባት እገዳ ወይም መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ የተላለፈ ውሳኔ ለምን ያህል ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል?
4. በመረጃ ስርዓት ውስጥ መመዝገብ ምን ማለት ነው?
5. ስላንተ የሚገልጹ መረጃዎች ከ E&S እና SIS የተባሉት የመረጃ ስርዓቶች የሚሰረዙት መቼ ነው?
6. የመግባት እገዳ እያለህ ኔዘርላንድ ውስጥ ብትኖርስ ምን ይደረጋል?
7. የመግባት እገዳ ወይም በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔን የማትስማማበት ከሆነ ምን ማድረግ ትችላላህ?
8. እንደገና ወደ ኔዘርላንድ መግባት የምትችለው መቼ ነው?
9. የመግባት እገዳ ወይም መረጃህን በመረጃ ስርዓት እንዲመዘገብ በሚመለከት የሚተላለፍ ውሳኔን (ግዝያዊ) እንዲነሳልህ እንዴት መጠየቅ ትችላለህ?
10. ጥያቄ ካለህ ምን ማድረግ አለብህ?


## 1. የመግባት እገዳ ምንድን ነው?

የመግባት እገዳ ከተጣለብህ፣ ለተወሰነ ጊዜ ወደ አውሮፓ ኅብረት (EU) ኣገሮች፣ ወደ አውሮፓ ኢኮኖሚያዊ ክልል (EER) ኣገሮች እና ወደ ስዊዘርላንድ መግባት ኣና ብእነኝህ ኣገሮች ውስጥ መኖር ኣይፈቀድልህም። የ EU እና የ EER ሀገራት የተኞች እንደሀኑ ለማየት www.ind.nl/eueer እና www.ind.nl/en/eueea በመጎብኘት ማየት ትችላለህት። እነዚህን ሁሉ አገሮች የአውሮፓ ኅብረት ብለን እንጠራቸዋለን። የመግባት እገዳው ለአየርላንድ የሚመለከት ኣይደለም።

ልትመለስ ውሳኔ ከተሰጠህ በኋላ ብቻ ነው የመግባት እገዳ የሚወሰንልህ። ይህ ውሳኔ በኔዘርላንድ እንድትኖር እንደማይፈቀድልህ እና ከነዘርላንድ መውጣት እንዳለብህ የሚገልጽ ውሳኔ ነው። እናም በውሳኔው ወደ ተጠቀሰው ሀገር መመለስ አለብህ። ወይም ከ አውሮፓ ኅብረት ውጭ (አየርላንድን ኣያጠቃልልም) ወደ ልትትኖርበት የሚፈቀድልህ ሌላ አገር መሄድ ኣለብህ ማለት ነው።

## 2. በመረጃ ስርዓት ውስጥ መመዝገብ ምንድን ነው?

በመረጃ ስርዓት ውስጥ የመመዝገብ ውሳኔ እና የመግባት እገዳ ተመሳሳይ ናቸው። በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ ከተወሰነልህ ወደ አውሮፓ ኅብረት ኣገሮች መግባት ኣና ብእነኝህ ኣገሮች ውስጥ መኖር ኣይፈቀድልህም። ላንተ የተሰጠህ በመረጃ ስርዓት ውስጥ የመመዝገብ ውሳኔ ለኔዘርላንድ ብቻ የሚመለከት ሊሆን ይችላል። በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ የሚወሰነው ኣንተ ለኔዘርላንድ አደገኛ ነህ ተብሎ ከታመነበት ነው።

## 3. የመግባት እገዳ ወይም መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ የተላለፈ ውሳኔ ለምን ያህል ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል?

የመግባት እገዳውን ወይ መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔን ለምን ያህል ግዜ እንደሚቆይ የሚወስነው ያንተ ሁኔታ ነው። በሚሰጠህ የውሳኔ ጽሁፍ የመግባት እገዳውን ወይ መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ የተወሰነልህ ለምን ያህል ግዜ እንደሚቆይ ተገልጿል።

የመግባት እገዳውን ወይ መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔ የሚጀምርበት ጊዜ ከአውሮፓ ኅብረት የወጣህበት ቀን ነው። መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ የተሰጠህ ውሳኔ ለኔዘርላንድ ብቻ የሚመለከት ከሆነ ግዜው የሚጀምረው ከኔዘርላንድ የወጣህበት ቀን ነው። IND ከነዘርላንድ ወይም ከኣውሮጳ ህብረት እንደወጣህ ካወቀ በኋላ እና የመግባት እገዳውን ወይ መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔን ግዜው ካበቃ በኋላ የመግቢያ እገዳውን ይሰረዝልሃል።

እንዲህ ባለ ሁኔታ ስምህን ከመረጃ ስርዓት ይሰረዝልሃል ማለት ነው፤ ከዛ በኋላ እንደገና ወደ ኔዘርላንድ እና ወደ ሌሎች የአውሮፓ ኅብረት አገሮች እንድትጓዝ ይፈቀድልሃል። IND ከኔዘርላንድ እንደወጣህ ማወቅ የሚችለው መረጃህን ከመረጃ ስርዓት እንዲሰረዝልህ ማመልከቻ ካቀረብክ በኋላ ነው። በጥያቄ ቁጥር 4 ውስጥ መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ መመዝገብ ምን እንደሆነ ማንበብ ትችላለህ።

## 4. በመረጃ ስርዓት ውስጥ መመዝገብ ምን ማለት ነው?

የመግባት እገዳ እንደተጣለብህ በመረጃ ስርዓት ውስጥ ትመዘገባለህ። ይህ ማለት መንግስት የግል መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ ያሰፍራል ማለት ነው። በዚህ መንገድ የድንበር ጠባቂዎች እና ፖሊሶች የመግባት እገዳ እንደተጣለብህ ወይም መረጃህን በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንዲመዘገብ እንደተወሰነልህ ለማየት ይችላሉ። በፍተሻ ግዜ እንዳትገባ ሊከለክሉህ ይችላሉ። እንዲህ ባለ ሁኔታ ወደ'ዛ ሀገር መግባት አይፈቀድልህም ማለት ነው። በሚሰጥህ የውሳኔ ጽሁፍ ላይ አንተ በየትኛው የመረጃ ሥርዓት ውስጥ እንደተመዘገብክ ይገለጻል።

2 የተለያዩ የመረጃ ስርዓቶች አሉ፥

- Executie & Signalering (E&S): ይህ የኔዘርላንድ ፖሊሶችና ድንበር ጠባቂዎች የሚጠቀሙበት የመረጃ ሥርዓት ነው።
- Schengeninformatiesysteem (SIS): ይህ የአውሮጳ የመረጃ ስርዓት ሆኖ የሸንገን ሀገራት የድንበር ጠባቂዎች እና ፖሊሶች የሚጠቀሙበት የመረጃ ሥርዓት ነው። የሼንገን አገሮች የትኞቹ እንደሆኑ በ www.ind.nl/schengengebied ወይም www.ind.nl/schengenarea ላይ ማንበብ ትችላለህ።

በ1 የመረጃ ስርዓት ውስጥ ብቻ ነህ መመዝገብ የምትችለው። የመግባት እገዳ ወይም ወደ መጣህበት ለመመለስ በሚመለከት በ SIS ትመዘገባለህ። በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ ከመወሰኑ በፊት የመግባት እገዳ ይጣልብሃል።

*በመረጃ ሥርዓት ውስጥ መጀመርያ የሚመዘገብ እንድትመለስ ውሳኔ ኣንደተሰጠህ ነው*

የመግባት እገዳ እንደተጣለብህ ወዲያውኑ አይመዘገብም። ማለትም መጀመሪያ እንድትመለስ ውሳኔ እንደተሰጠህ በSIS ይመዘገባል። ከአውሮፓ ኅብረት ከወጣህ እናም IND ይህንን የሚያውቅ ከሆነ ምዝገባውን የመግባት እገዳ እንደ ተጣለብህ ይቀየራል። ይህ ማለት ደግሞ ወደ አውሮፓ ኅብረት እንድትጓዝ እና በአውሮፓ ኅብረት ውስጥ እንድትኖር አይፈቀድልህም ማለት ነው። በSIS የመመዝገብ እና ወደ መጣህበት የመመለስ ውሳኔ በሚመለከት በ www.ind.nl/nl/terugkeerbesluit ወይም www.ind.nl/en/return-decision ተጨማሪ ማንበብ ትችላለህ።

*በመረጃ ሥርዓት እንድትመዘገብ እና የመግባት እገዳ ውሳኔ*

ውሳኔውን በመረጃ ሥርዓት እንድትመዘገብ ብቻ የሚል ሊሆን ይችላል። ኣንዲሁም ውሳኔውን በመረጃ ሥርዓት እንድትመዘገብ እና የመግባት እገዳ እንደተጣለብህ ያጠቃለለ ሊሆን ይችላል።

*በአውሮፓ ኅብረት የመኖር መብት ማግኘት እና የመግባት እገዳ እንደተጣለብህ በመረጃ ስርዓት እንድትመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔ*

በአንድ የአውሮፓ ኅብረት ኣገር የመኖር መብት የተሰጠህ ከሆንክ እንዲሁም የኔዘርላንድ መንግስት ከ2 አመት በላይ የመግቢያ እገዳ የጣለብህ ከሆንክ እናም በመረጃ ሥርዓት እንድትመዘገብ የተወሰነልህ ከሆንክ በዚህ ሁኔታ የመኖሪያ መብትህን እንድትሽር ኔዘርላንድ ለዛ የአውሮፓ ኅብረት አገር ትጠይቃለች። ያቺ የአውሮፓ ኅብረት አገር የመኖሪያ መብትህን ከሻረች በSIS ውስጥ እንድትመለስ እንደ ተወሰነልህ እና የመግባት እገዳ እንደተጣለብህ ብቻ ይመዘገባል። የመኖሪያ መብትህን ካልተሻረ ደግሞ IND የመግቢያ እገዳህን ያነሳል። ከዛም ኣንተ የምትመዘገበው E&S በተባለው የመረጃ ስርዓት ነው። ያቺ የአውሮፓ ኅብረት አገር የመኖሪያ መብትህን ከግዜ በኋላ ከሻረች ደግሞ፣ IND ላንተ SIS በተባለው የመረጃ ስርዓት ነው የሚመዘግብህ።

## 5. ስላንተ የሚገልጹ መረጃዎች ከ E&S እና SIS የተባሉት የመረጃ ስርዓቶች የሚሰረዙት መቼ ነው?

- የተጣለብህ የመግባት እገዳህ ወይም በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔን ግዜው እንዳለቀ እርግጠኛ ከሆነ። እናም አንዴ ከሄድክ በኋላ ወደዚህ ያልተመለስክ ከሆንክ።
- የመግባት እገዳ ከተጣለብህ በኋላ IND ኣንተ በሌላ የአውሮፓ ኅብረት አገር የመኖሪያ መብት እንደተሰጠህ ካወቀ። ከዚያም IND የመግቢያ እገዳህን በማንሳት መረጃህን ከ SIS ይሰርዘዋል። ለህዝባዊ ስርዓት ስጋት መሆን ትችላለህ ተብሎ ከታሰበ ደግሞ መንግስት ሌላ እርምጃ ሊወስድልህ ይችላል። እንዲህ ባለ ሁኔታ መረጃህን E&S በሚባል የመረጃ ስርዓት ውስጥ ይመዘገባል።
- የተጣለብህ የመግቢያ እገዳ ወይም በመረጃ ስርዓት እንድትመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔ እንዲነሳልህ ማመልከቻ ያቀረብክ ከሆነ እና ይህ ማመልከቻ ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ። በጥያቄ ቁጥር 9 የመግቢያ እገዳህ እንዲነሳልህ እንዴት ማመልከቻ ማቅረብ እንደምትችል ተገልጿል። የመግቢያ እገዳውን ለጊዜው ከተነሳልህ መረጃህን በ SIS ተመዝግቦ ይቆያል።

## 6. የግባት እገዳ እያለህ ኔዘርላንድ ውስጥ ብትኖርስ ምን ይደረጋል?

የመግባት እገዳ ወይ በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ ውሳኔ ከተሰጠህ በኋላ ኔዘርላንድ ውስጥ መኖር በህግ ያስቀጣል። እስከ 6 ወር የሚደርስ የእስራት ውሳኔ ሊፈረድብህ ይችላል ወይም በሺዎች ዩሮ የሚቆጠር የገንዘብ ቅጣት ልትቀጣ ትችላለህ። ይህም በወንጀል መቅጫ ሕጉ በአንቀጽ 197 እና በስደተኞች ሕጉ በአንቀጽ 108 ላይ በዝርዝር ተገልጿል።

### 7. የመግባት እገዳ ወይም በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔን የማትስማማበት ከሆነ ምን ማድረግ ትችላለህ?

ይህ በአንተ ሁኔታ ላይ የሚመሰረት ነው። ወደ IND ተቃውሞ ማቅረብ ወይም ለፍርድ ቤቱ ይግባኝ ማለት ትችላለህ። በተሰጠህ ውሳኔ ውስጥ ይህንን እንዴት ማድረግ እንደምትችል ተገልጿል።

### 8. እንደገና ወደ ኔዘርላንድ መግባት የምትችለው መቼ ነው?

- የመግባት እገዳ ወይ በመረጃ ስርዓት ውስት እንድትመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔን ግዜው ያበቃ ከሆነ።
- ይህ የሚሆነው ኣንተ ራስህ የመግባት እገዳ ወይ በመረጃ ስርዓት ውስት እንድትመዘገብ በሚመለከት የተላለፈ ውሳኔን እንዲነሳልህ ከጠየቅክ እና ማመልከቻህን ተቀባይነት ካገኝ ብቻ ነው።

### 9. የመግባት እገዳ ወይም መረጃህን በመረጃ ስርዓት እንዲመዘገብ በሚመለከት የሚተላለፍ ውሳኔን (ግዝያዊ) እንዲነሳልህ እንዴት መጠየቅ ትችላለህ?

የመግባት እገዳ ወይ በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ የተላለፈ ውሳኔን እንዲነሳልህ መጠየቅ ትችላለህ? ለምሳሌ የመግባት እገዳ ወይም በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ የተላለፈውን ውሳኔን ገና ሳይጠናቀቅ ወደ ኔዘርላንድ መግባት ያለብህ ከሆንክ። በጣም ልዩ እና አስቸኳይ በሆኑ ሁኔታዎች የመግባት እገዳ ወይም በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ የተላለፈውን ውሳኔን ግዝያዊ እንዲነሳልህ መጠየቅ ትችላለህ።

ለምሳሌ የመግባት እገዳ ወይም በመረጃ ስርዓት ውስጥ እንድትመዘገብ የተላለፈውን ውሳኔን ያበቃ ከሆነ። እንዲሁም IND በ E&S ተመዝግበህ እያለህ ኔዘርላንድን ለቅህ እንደ ወጣህ የማያውቅ ከሆነ። ወይም IND በ SIS ተመዝግበህ እያለህ ነገር ግን የአውሮጳ ህብረት ለቅህ እንደ ወጣህ የማያውቅ ከሆነ።

ይህንን ለማድረግ ያልተፈለገ ባዕድ የሚል መግለጫ እንዲነሳልህ ወይም የመግባት እገዳ እንዲነሳልህ ለመጠየቅ የምትሞላውን ፎርም (9004 ወይም 9504) መሙላት ኣለብህ። ይህ ፎርም በድረ-ገጸችን ማግኘት ትችላለህ። ፎርሙን በመሙላት ወደ IND መላክ ኣለብህ። ሌላ ሰው ኣንተን በመወከል ይህንን እንዲነሳልህ ሊጠይቅልህ ይችላል። ይህ ለማድረግ ግለሰቡ ኣንተን ወክሎ እርምጃ እንዲወስድ ኣንተ ሕጋዊ ፈቃድ መስጠት አለብህ። ይህንን ወረቀት ላይ በማስፈር ፊርማህን በማኖር ነው የምታደርገው። ይህ ውክልና ስልጣን ተብሎ ይጠራል።

### 10. ጥያቄ ካለህ ምን ማድረግ አለብህ?

- www.ind.nl/ongewenstverklaring ወይም www.ind.nl/en/undesirability የሚሉ የኛ ድረ ገጾች ጎብኝ።
- ወደ የ IND የመረጃ መስመር፣ ስልክ ቁጥር +31 88 043 04 30 ደውል። ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 09:00 ሰዓት እስከ 17:00 ሰዓት ድረስ ባለው ግዜ መደወል ትችላለህ።

*ከዚህ ጽሑፉ ይዘት ምንም ዓይነት መብት ማግኘት አይቻልም። ትርጉሙ ወደ ትርጓሜ ልዩነት የሚያመራ ከሆነ በኔደርላንድስ ቋንቋ የተዘጋጀውን ጽሁፍ ነው ወሳኝ የሚሆነው። ምንጩ በመጥቀስ እዚህ እትም ላይ የሚገኘውን ጽሑፍ ለሌላ ጥቅም ሊውል ይችላል።*